## አለም አቀፍ ኔትወርክ ለህዝብ ትምህርት ቤቶች (INPS):

Francis C. Hammond International Academy ከአለም አቀፍ ኔትወርክ ለህዝብ ትምህርት ቤቶች ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር "አለም አቀፍ አቀራረብ" (*“Internationals Approach.”*) የተባለ ስኬታማ የማስተማሪያ እና የመማሪያ ሞዴል ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እያቀረበ ነው።

- በዩናይትድ ስቴተስ ውስጥ 27 አለም አቀፍ ኔትወርክ ትምህርት ቤቶች አሉ።
- በተደራጁ የኤንዋይሲ አካባቢ ካሉ ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነጻጸር እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከእጥፍ በላይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን እያስመረቁ ይገኛሉ።
- የአለም አቀፍ ኔትወርክ አላማ ሁሉም በቅርብ የመጡ ስደተኛ ተማሪዎች ጥራት ላለው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በማግኘት ለኮሌጅ፣ ለስራ እንዲዘጋጁ፣ እንዲሁም በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ ለአሜሪካን ህልማቸው በር እንዲከፍቱ ማረጋገጥ ነው።

የበለጠ መረጃ በዚህ ድረገጽ ያግኙ። www.internationalsnps.org

## Francis C. Hammond International Academy

### ራዕይ

አለም አቀፍ ተማሪዎች ለተለያዩ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ በሁዋላ ላሉ እና ለስራ እድሎች እንዲዘጋጁ የሚያስችላቸውን እውቀት እና ክህሎቶች እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

አለም አቀፍ አካዳሚ የሚያንጽ የመማሪያ ሁኔታ ሲኖረው ተማሪዎች ጥልቀት ያለው ይዘት እና የቋንቋ አላማዎችን በመተባበር፣ በመጠያየቅ፣ እና በመዳሰስ መልክ ያገኛሉ።

Francis C. Hammond Middle School ቤት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ መማር ማስተማር በመሃከለኛ ደረጃ ሞዴል የሆነ ነው።

### አላማ

የአለም አቀፍ አካዳሚ (IA) Francis C. Hammond Middle Schoolቤት አላማ በዩናይትድ ስቴተስ ውስጥ ላለው ህይወት ባሉት በአካዳሚክ፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ሽግ ግሮች ተማሪዎችን መደገፍ ነው። የምንጠቀመው በጥናት ላይ የተመሰረቱ እና ከአለም አቀፍ አቀራረብ ጋር የተጣጣሙ ተግዳሮቶችን ሲሆን እነዚህም የቋንቋ እና ይዘት ማስተማርን ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በማዋሃድ የማህበረሰባቸው ጠቃሚ አባላት እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው።

# Francis C. Hammond Middle School

# አለም አቀፍ አካዳሚ



**ማህበረሰብ**

**መተባበር**

**ቁርጠኝነት**

http://blogs.acpsk12.org/hammondia/

## ፈጣን መረጃዎች ስለ
## FCH አለም አቀፍ አካዳሚ (IA)

- IA አስተማሪዎች የተማሪዎችን አካዳሚ አይነት እያስተማሩ በተመሳሳይ ጊዜ የተማሪዎች የአካዳሚክ ቋንቋ መማርን ለመደገፍ በከፍተኛ ሁኔታ የሰለጠኑ ናቸው።

- IA ተማሪዎች በFrancis C. Hammond Middle Schoolለሁሉም ኢሌክቲቭ፣ የጤና፣ እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ክፍሎች ማግኘት ይችላሉ።

- IA ተማሪዎች የሚማሩት የተለያዩ ፕሮጄዎች ላይ የተደባለቁ የቋንቋ ደረጃ ባላቸው እና የአፍ መፍቻቸው በሆኑ ተማሪዎች ጋር በመሆን ነው።

- IA ክፍሎች የተለያዩ የእንግሊዝኛ ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች በማደባለቅ የቋንቋ እና ይዘት እድገታቸውን ያፋጥናል። ተማሪዎች አሁን ባላቸው የእንግሊዝኛ ብቃት ብቻ ወደ ክፍሎች አይመደቡም።

- IA ተማሪዎች ለነሱ የተዘጋጀ አማካሪ እና አስተዳዳሪ ሲኖራቸው ይህም ለአገሪቱ አዲስ ለሆኑ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ያሉዋቸው ፍላጎቶች ላይ ያተኩራሉ።

- IA ተማሪዎች አማካሪ ሲመደብላቸው ይህም ተማሪዎችን ለመምራት እና ለነሱ ለመሙዋገት ይሰራል።

- በያንዳንዱ የትምህርት አመት መጨረሻ ላይ፣ የ FCH-IA ቡድን የያንዳንዱን ተማሪ ምደባ በማየት ከወላጆች ጋር በመተባበር ለልጃቸው የሚስማማውን የአካዳሚክ ሁኔታ ይወስናሉ።

## አለም አቀፍ አካዳሚን ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?





**የተማሪዎቻችን ቃላቶች…..**

በ 2016 በተሰናዳው የተማሪ ዳሰሳ ጥናት መሰረት፣ በዚህ አመት ላይ ምን እንደረዳቸው ሲጠየቁ፣ የአለም አቀፍ አካዳሚ ተማሪዎቻችን ያሉት…

- “በአለም አቅፍ አካዳሚ ውስጥ ሁሉም ነገር አስደናቂ እንደሆነ አስባለሁ”

- “ጓደኞቼ እና አስተማሪዎቼ… ሁልጊዜ እየረዱን ነው፣ እናም እንግሊዝኛን ከጓደኞቼ ጋር እየተማርኩ ነው።”

- “ሁሉም አስተማሪዎቼ ለኔ እንደሚያስቡ ነው። እንዲሁም ያዳምጡኛል።”

- “እንደማስበው ከሁሉም በላይ የረዳኝ በትምህርት አመቱ የሰራሁዋቸው ሁሉም ፕሮጀዎች ናቸው።”

## የ FCH አለም አቀፍ አካዳሚ ቡድንን ያግኙ

**IA አስተባባሪ:** ቲሞቲ ብራነን
timothy.brannon@acps.k12.va.us
703-461-4046

ስለ ማስተማሪያ ፕሮግራሙ ወይም ስለ ልጅዎ ምደባ በአለም አቀፍ አካዳሚው ጥያቄዎች ካለዎት ሚስተር ብራነንን ያግኙ

**IA ትምህርት ቤት አማካሪ**: ካቲ ሚግሊዮርኒ
katie.migliorini@acps.k12.va.us
703-751-0539

ስለተማሪዎ የክፍል የጊዜ ሰሌዳ፣ የተማሪዎ ውጤቶች፣ የተማሪዎ ስሜታዊ ጤና እና ደህንነት፣ ወይም ስለማንኛውም የቤተሰብዎ ፍላጎቶች፣ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ላለዎት ጥያቄዎች ሚስ ሚግሊዮርኒን ያግኙ

### ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች ተጨማሪ ድጋፎች

አዲሱን ስርአት ለመዳሰስ ሲሞክሩ ቤተሰብዎ ሊያጋጥመው የሚችሉትን ልዩ ችግሮችን እንረዳለን። በትምህርት ቤታችን እና በአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ልዩ ፍላጎቶች መርዳት የሚችሉ ብዙ ድጋፎች አሉን። እባክዎትን ርዳታ ከፈለጉ፣ ያግኙን፤ የሚፈልጉትን እንዲያገኙ ለማገዝ ደስተኞች ነን። ከአጋሮቻችን የተወሰኑት እነዚህን ይጨምራሉ፥

- **በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦች (CIS) የ NOVA**
- **የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ (FACE) ማእከል**
  www.acps.k12.va.us/face-centers
- **ኖርዘርን ቨርጂኒያ የቤተሰብ አገልግሎቶች**